# ኢትዮጵያ ከካርቦን ሽያጭ በየዓመቱ 3.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ የማግኘት አቅም አላት

*ጌታቸው ትሰፋዬ*
*ብዝሀ ሕይወጥ ጥበቃ ኢንስቲትዩት*

የአካባቢ አየር ሙቀት መጨመር አሳሳቢነቱ እየጐላ በመምጣቱ ይህንን ሥጋት ለመቆጣጠር በከባቢ አየር ውስጥ ያለውን የግሪን ሀውስ ጋዞች ክምችት ለመቀነስ እንዲረዳ የካርቦን ሽያጭ ሥርዓትን መዘርጋት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡

የካርቦን ሽያጭ ሥርዓት የበለጸጉ ሀገራት በኢንዱስትሪዎቻቸው አማካይነት በቀጥታ ወደ ከባቢ አየር የሚለቁትን የግሪን ሀውስ ጋዝ (በተለይም ካርቦን ዳይ-ኦክሳይድ የተባለውን ውህድ) ታዳጊ ሀገራት በየአካባቢዎቻቸው የሚያደርጉት የደን ልማት ሥራዎች ወደ ከባቢ አየር የገባውን የካርቦን ጋዝ በዛፎችና በአነስተኛ ዕፀዋቶች አማካይነት ወደ ሰውነታቸው ገብቶ በዚያው እንዲከማች በማድረግ፣ በከባቢ አየር ውስጥ ያለውን የካርቦን መጠን በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ የሚደረግበት የግብይት ሥርዓት ነው፡፡

የዚህ የካርቦን ገበያ ሥርዓት መፈጠር በዓለም አቀፍ ደረጃ መጓተት እያሳየ ቢሆንም ሀገራችን በዘርፉ ያላትን አቅም መፈተሽና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን አስቀድሞ መቃኘት በድርድር ሂደቱ ላይ በትኩረት ለመንቀሳቀስ ይረዳል፡፡

በመሆኑም ሀገሪቱ ባላት የተፈጥሮ ደኖች ላይ እስካሁን የተደረጉ የናሙና ጥናቶች ዘርፉ ከፍተኛ ዋጋ ያለው የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኝ እንደሚችል ይጠቁማል፡፡

ኢትዮጵያ አሁን ያላት የደን ሽፋን 4.79 ሚሊዮን ሄክታር ሲሆን ይህም ወደ 42.2 ሚሊዮን ቶን ካርቦን ጋዝ ከከባቢ አየር ውስጥ በየዓመቱ ያስወግዳል፡፡ ይህም በካርቦን የገበያ ዋጋ ሲሰላ በየዓመቱ 1.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ያስገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ዋዜማ «ሁለት ዛፍ በሁለት ሺህ» በሚል ቃል ወደ 1 ቢሊዮን የሚጠጉ የዛፍ ችግኞች በመላ ሀገሪቱ ተተክለዋል፡፡ እነዚህ ተክሎች በየዓመቱ 2.5 ሚሊዮን ቶን ካርቦን ጋዝ ከከባቢ አየር የሚያስወግዱ ሲሆን በገንዘብ ሲተመን 113 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይደርሳል፡፡

ከሚሊኒየሙ ተሞክሮና ልምድ እንደታየው ሀገራችን በቀጣይ ጊዜያት ወደ 17 ቢሊዮን ሀገር በቀል የዛፍ ችግኞችን ብትተክል በየዓመቱ ወደ 44.85 ሚሊዮን ቶን ካርቦን ከከባቢ አየር የማስወገድ አቅም ይኖራቸዋል። ይኸም ከካርቦን ሽያጭ ዋጋ 1.7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተጨማሪ ገቢ በየዓመቱ ያስገኝላታል። ይህ መጠን የአሜሪካን ዓመታዊ የካርቦን ልቀት 13 በመቶ ድርሻ የሚሸፍን ይሆናል። 17 ቢሊዮን የዛፍ ችግኝ መትከል ዓመታዊ የካርቦን ሽያጭ ገቢን ወደ 3.3 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከፍ የሚያደርግ ሲሆን፣ የሀገሪቱን የደን ሽፋንም ከ4 በመቶ ወደ 8 በመቶ ያሳድጋል።

በመሆኑም መንግሥት ለካርቦን ሽያጭ ገበያ መፈጠር በተያያዘው ተነሳሽነት አጠናክሮ እንዲቀጥልበትና፣ ሀገራችን ያላት እምቅ የተፈጥሮ ሀብትና የቅርብ ጊዜ የሕዝብ ተሞክሮ ሲታከል ይህንን አዲስ የገበያ ሥርዓት የበለጠ ምርታማና የገቢ ማስገኛ ዘርፍ ማድረግ እንደሚችል በቂ ማስረጃዎች ናቸው።